# ኢትዮጵያን ከቀውስ ሕዝባችን ከአስከፊ አደጋ ለመከላከል በጋራ እንቁም
# ሁሉን አቀፍ የምክክር ጥሪ

ቀን፤ ጳጉሜ 2፣ 2008 ሴፕቴምበር 07፣ 2016

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ25 ዓመታት የህወሃት አናሳ ቡድን የዘረኝነት የጭካኔ አገዛዝና፤ ተዘርዝሮ የማያልቅ ግፍ፣ ስቃይ፣ በደልና የጥቃት ሰለባ ገፈት ቀማሽ በመሆን ከቆየ በኋላ ከዳር እስከዳር ተነስቶ የነዚህ የጥቂት ጎጠኞች መሰሪ ስርዓትን በመቃወም በቃኝ ያለበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ መላው ዓለም እየመሰከረ ይገኛል። ከወራቶች በፊት በኦሮሞ ሕዝብ በክልሉ ዙሪያ ተጀምሮ የነበረው ሕዝባዊ እምቢተኝነትና እንቅስቃሴ ከሐምሌ ወር ጀምሮ ደግሞ በጎንደር ከተማና በአካባቢው ተቀጣጥሎ በአሁኑ ሰዓት በከፍተኛ ደረጃ ተጋግሎ በመላው ጎጃምና ጎንደር እንዲሁም በሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች እየተስፋፋ ይገኛል።

ይህ የሕዝባዊ እምቢተኝነትና አመጽ በራሱ በሕዝቡ የተነሳሳና የሚመራ፤ የሕዝብ ግፍና በደል የወለደው የማንም የውስጥም ሆነ የውጭ ኃይል እጅ የሌለበት ኢትዮጵያውያን በመላው የአገሪቱ ክፍል የሚያካሂዱት ሙሉ ለሙሉ ፍትሐዊ የሆነ ሕዝባዊ ትግል ነው። የዘረኛው ህወሃት መራሹ ስርዓት ለሕዝብ ጥያቄ መልስ በመስጠት ፈንታ በጉልበትና በመሳሪያ ኃይል የሕዝብን መነሳሳት ለመጨፍለቅ በሚያደርገው ጥረት የብዙ ወገኖቻችንን ሕይወት እየቀጠፈና የለየለትና ይፋ የሆነ የሕዝብ እልቂት የማድረስ ወንጀል እየፈጸመ ይገኛል። አንድ አገዛዙ ያልተገነዘበው ወይንም ሊገነዘበው ያልፈለገው ጉዳይ ግን ሕዝባችን ከፍተኛ መስዋዕትነት ለመክፈል እንደቆረጠና ከአሁን ወዲህ ወደ ኋላ የማይልበት ደረጃ ላይ መድረሱን ነው። ይህ ከጅምሩ ኋላ ቀርና ዘረኛ የሆነው በጥቂቶች የበላይነት የሚመራው የህወሃት አገዛዝ ጊዜው ያለፈበትና የሕዝባችንን የነጻነትና የፍትህ ስርዓት ጥማት ሊመጥን የማይችል በ21ኛው ክፍለ ዘመን አሁንም ሕዝብን እንደለመደው በመሳሪያ ኃይልና በጫካ ሕግ ሊገዛ የሚዳዳው ያረጀ ያፈጀና ራሱም እንዳመነው 'የበሰበሰና' ከስሩ መነቀል ያለበት ስርዓት ነው።

በአሁኑ ሰዓት ለሕዝብና ለሃገር ደንታ የሌለው የህወሃት አመራር ሕዝባዊ ተቃውሞው ሥልጣኑን ሊያሳጣኝ ነው ከሚል ፍራቻ፤ በመጨረሻው ሰዓት ማንኛውንም አይነት ጭካኔ የተመላበት ያለ የሌለ ኃይል ከመጠቀም ወደ ኋላ አልልም በማለት፤ ከፋሺስታዊና አምባገነናዊ ባህሪው በመነሳት በተለይ በጎንደርና በጎጃም፣ እንዲሁም በወሎና በተለያዩ የኦሮሞ ክልሎች በከባድ መሳሪያ ጭምር የተደገፈ አሰቃቂ እልቂትና ወንጀል በሰላማዊው ሕዝብ ላይ እየፈጸመ ይገኛል። ይህ እርምጃ በይፋና በሰፊው የቀጠለውም የህግ ከለላ ያለው ለማስመሰል ጠቅላይ ሚ/ር ተብዬው "ለፀጥታ ኃይሎች ትዕዛዝ ሰጥቻለሁ" ብሎ በመገናኛ ብዙሃን ሃላፊነት የጎደለው መግለጫ እንዲሰጥ ከተደረገ በኋላ መሆኑ ብዙዎችን በጣም ያሳዘነና ያስቆጣ ነው።

አገዛዙ ለሚፈጸመው ጥቃትና ሽብር ሰለባ የሆነው ህዝብ ራሱንና ቤተሰቡን ከሚደርስበት ግድያና አፈና ለመከላከል ባልሞት ባይ ተጋዳይነት በእጁ ያለውን ማንኛውንም መሳሪያ ቢጠቀም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም። ሕዝቡ እየተሰነዘረበት ላለው ጥቃት መከላከልና ምላሽ መስጠት እንጂ ምንም ዓይነት አላግባብ የሆነ ጥቃት በተወሰነ ሕዝብም ላይ ሆነ በታጠቀው የአጋዚ ጦር ላይ አልሰነዘረም፤ ይልቁንም አኩሪ በሆነ የነጻ ህዝብ ተጋድሎና ተከባብሮ በመኖር ጨዋ ታሪኩ ላይ ተመስርቶ በከፍተኛ ጥንቃቄና ትዕግስት የግፍና የዘረኛ አገዛዝ በቃኝ እያለ በተለያዩ ሰላማዊ መንገዶች ብሶቱንና እምቢተኝነቱን ሲገልጽ ቆይቷል፤ እየገለጸም ነው።

የአካባቢው ሕዝብ ከማንም በላይ የዘረኛውን ቡድን ተንኮልና መሰሪ አካሄድ ጠንቅቆ የሚረዳና የሚያውቅ ነው። ዛሬ ሕዝቡ የራሱን የጎበዝ አለቃ በመምረጥ በጥንቃቄና በስልት እየተንቀሳቀሰ ነው። ከማንኛውም በርቀት ከሚገኝ አካል የሚፈልገው ነገር ትግሉ እንዴት መካሄድ እንዳለበት መመሪያና ትእዛዝን ሳይሆን፤ አጋር ነኝ የሚለው ተቃዋሚ ኃይል በሙሉ አንድ ላይ በማበር "ሁሉም ነገር ለሕዝባዊ እምቢተኝነት ድጋፍና ለስርዓት ለውጥ" በሚል መፈክር ዙሪያ በመተባበርና በመሰባሰብ፣

- የሕዝባዊ ዓመጹን በተግባር የሚያግዝ የሞራል፣ የፋይናንስና የቁሳቁስ ድጋፍ መስጠት፤
- የዘረኛው ቡድን አገዛዝ በሕዝብ ላይ እየፈጸመ ያለውን ወንጀል ለዓለም ዓቀፍ የዜና ማሰራጫዎች በሰፊው እንዲዘገብና እንዲሰራጭ ማድረግ፣
- ለዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋማትና መንግሥታት በአገዛዙ የሚፈጸመውን ወንጀል በማሳወቅ በስርዓቱ ላይ በቀጣይነት ጫና እንዲያደርጉና፤ ሕዝባችን እየጨረሰ ላለው አገዛዝ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲ፣ ወታደራዊና ሌላም ድጋፍ ከመስጠት እንዲታቀቡ፤ ሕዝባችን ከሚያካሂደው ፍትሐዊ ከሆነ የነጻነት የትግል ጎን እንዲቆሙና፤ ጊዜና ዘመን ያለፈበትን የሕወሃት/ኢህአዴግ ዘረኛ አገዛዝ ተጨማሪ የንፁሃን ደም ከማፍሰስ ተቆጥቦ ስልጣኑን ለሕዝብ እንዲያስረክብ ተጽእኖ እንዲያሳድሩ ማሳሰብ፤
- ሁሉንም በአገሪቱ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ባለድርሻዎች (የፖለቲካ፣ የሲቪክና ሌሎችም ሕዝባዊ ተቋማት) የሚያሳትፍ የሀገራችንን ጥቅም የማያስደፍር ፣ የህዝባችንን አንድነት የማያናጋ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ተቃዋሚዎች ባንድነት እንዲቆሙ ተጽእኖ ለማሳደር በተግባር መንቀሳቀስን ነው።

በተጨማሪም አሁን ያለንበት ወቅት የግፍ አገዛዝ በቃን፣ በዘረኞች መገዛት በቃን ብሎ የተነሳው ቆራጡ ህዝባችንን በስርአቱ ከተሰነዘረበት እልቂት ለመታደግና በአሸናፊነት እንዲወጣ ለማስቻል፤ ከሀገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአንድ ላይ በመሰባሰብ ሊያበረክቱ የሚችሉትን መጠነ ሰፊ ዕምቅ የኃይል ድጋፍ፣ ሊጫወቱ የሚችሉትን ወሳኝ የሆነ ሚና ያገናዘበና ለዚያም የሚመጥን ሚዛን የሚደፋ ስራ በአንድነትና በህብረት የመስራት ሀላፊነት ከምንጊዜውም በላይ በላያቸን ላይ እንደወደቀ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

አሁን በመካሄድ ላይ የሚገኘው ህዝባዊ እምቢተኝነት ጉልበቱ እንዲጨምር፣ በመላ ሀገሪቱም በፍጥነት እንዲስፋፋ፣ ትግሉም ከዳር እስከዳር ይበልጥ እንዲቀነባበር የሚቻለውን ሁሉ ለማድረግ በአስቸኳይ ምክክር በማድረግ መረባረብ ያስፈልጋል። ትግሉ አሁን ካለበት ደረጃ እመርታዊ በሆነ መልክ አድጎ ብሔራዊ አድማስ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የሚገኝ ማንኛውም ዜጋ የትግሉ ባለቤትና_ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ጥረቱ መስፋፋት አለበት። ይህ ደግሞ ነገ ሳይሆን ዛሬ መደረግ ይገባዋል።

ከዚህም አኳያ ከላይ ባጭሩ በተዘረዘሩት መሰረታዊና ተያያዥ ገዳዮች ላይ የተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ስብስብ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋር ትግል ሸንጎ፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤትና የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ ተከታታይ ውይይቶች በማድረግና ቀደም ሲል የነበሩ ግንኙነቶችን በማጠናከር በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰናል፤

1ኛ/ በጋራ በመሆን በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን ከፍተኛ ሕዝባዊ ሰላማዊ የእምቢተኝነት ትግል ሙሉ በሙሉ በመደገፍ፣ ለዚህ ትግል አስፈላጊ የሆነውን ሁለንተናዊ ድጋፍ ለመስጠት በጋራ አጀንዳዎች ላይ አተኩረን ለመስራት ተስማምተናል።

2ኛ/ አሁን በመካሄድ ላይ ያለው የህዝብ እምቢተኝነት ለተፈላጊው የስርአት ለውጥ መሰረት እንደሆነ ጥርጣሬ የለንም። ከዚህ ጋር በተያያዘም ትግሉን ይበልጥ ለማጠናከርና ውጤቱንም ለማፋጠን፤ በተጨማሪም ሁሉንም በሚያሳትፍ እውነተኛና የተደላደለ የሽግግር ሂደት ዘላቂ ወደ ሆነ ሕገ መንግስታዊ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመሸጋገር ምን ማድረግ እንዳለብን መመካከር ወቅታዊና ተገቢ ተግባር ነው። ጊዜው ሁሉም ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያዊ እጅ ለእጅ ተያይዞ ሊነሳ የሚገባበት ነው። ጊዜው የትብብር ነው። በመሆኑም ይህን ሁኔታ ለመመርመርና አማራጮችን ለመፈተሽ ሁሉም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ኃይሎች የሚሳተፉበት ሰፊ የምክክር ጉባኤ መጥራት አጣዳፊ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ፤ ከሚመለከታቸውና ፈቃደኛ ከሆኑ ጋር በመተባባር በአስቸኳይ የሁሉም ባለድርሻዎች ጉባኤ ለመጥራት ተስማምተናል።

3ኛ/ ጉባኤውን በጋራ ለመዘጋጀት ፍቀደኛ የሆኑ ቡድኖችን፤ የምክክር ጉባኤው የሚካሄድበትን ጊዜና ቦታ ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ወደፊት እናሳውቃለን።

<u>**መልእክት፤**</u>

**ለኢትዮጵያ ህዝብ**
ከግፈኛወና ከዘረኛው የህወሀት መራሹ አገዛዝ ጋር እየተዋደቅህ ለምትገኘው <u>ኢትዮጵያዊ ወገናችን፤ </u>በምታካሂደው ተጋድሎና እየከፈልክ ባለኸው መስዋእትነት ዛሬም እጅግ የምንኮራብህ፣ እንደሆነ እንገልጻለን። በግፈኛው ስርአት እየተገደሉ፣ እየቆሰሉና ንብረትና ሀብታቸውን እያጡ ላሉ ሁሉ ያለንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጥን፣ ስማቸው በሀገራችን ታሪክ ምን ጊዜም ህያው ሆኖ ይኖራል። በምንችለው መንገድ ሁሉ ትግልህን ለመደገፍ፣ የወደቁ ጀግኖችን አርማ ከፍ አድርገን በማውለብለብ የተሰዉበት ዓላማ ግቡን እስኪመታ ትግላችን እንደምንቀጠል ቃልኪዳናችን እናድሳለን። ይህ ትግል በመላ ሀገሪቱ ተስፋፍቶ በሀገራችን ውስጥ የአምባገነን እና የዘረኛነት ስርአት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እስኪያከትም የተባባረ ትግላችን ይቀጥላል

**ለመከላከያ ሰራዊቱ**
የኢህአዴግ/ህወሃት አምባገነን እና ዘረኛ መሪዎች ላላፉት 25 አመታት ስልጣናቸውን በህዝባችን ላይ ለመጫን ሲጠቀሙብህ ቆይተዋል አሁንም ለተመሳሳይ ስግብግብ አላማቸው እየተጠቀሙብህ ነው። የኢህአዴግ/ህወሃት ባለስልጣኖች ቀጣይ ፍላጎት አንተንና ህዝቡን ለያይቶ ስልጣናቸውን ማራዘም ነው። የህዝቡ ትግል ያንተም ትግል ነው። የህዝቡ ነጻነት ያንተም ነጻነት ነው። አምባገነኖችና ዘረኞቹ የሕወሀት መሪዎች በወገንህ ላይ እንድትተኩስ የሚሰጡህን ትእዛዝ አትቀበል። የሀገር ድንበርን ከማስከበር ውጭ በሀገር ውስጥ በየትኛውም የሀገራችን ክልል በህዝብ ላይ አልዘምትም በል፤ በዚህ ሳምንት ውስጥ ህዝባዊ እምቢተኝነቱን በመቀላቀል አርኣያ እንደሆኑት የመከላከያ ሃይል ጓዶችህ ከህዝብ ጎን ቁም።

**ለኢህአዴግ አበላት**
ለ25 አመታት የተሰለፋችሁበት ድርጅት ኢህአዴግ እነሆ ህዝባችንን በተለያዩ መንገዶች በመከፋፈል፣ መብቱን በመርገጥ ሀገራችንን ወደከፋ አደጋ አድርሷታል። የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ዘረኛ ስርአት የደረሰበትን ጭቆና ከጀርባው ላይ አሽንቅጥሮ ለመጣል መራራ ትግል እያካሄደ ነው። ይህን ትግል በማገዝ ብዙዎቻችሁ በግልጽም በድብቅም ለምታካሂዱት ድጋፍ አድናቆታችን ከፍተኛ ነው። አሁንም ይህን ዘረኛ ስርአት ለማስወገድ ከህዝብ ጎን ተሰልፋችሁ ትግሉን እንድታፋፍሙ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ከህዝብ ጎን በመሰላፍ ታሪክ ስሩ፣ በበታችነት ከመኖር ተላቀቁ፣ የህዝባችን ከህወሃት መራሹ ዘረኛ አገዛዝ ነጻ መውጣት የናንተም ነጻነት ነው።

<u>**ለትግራይ ህዝብ**</u>
ትግራይ የኢትዮጵያ ታሪክ መሰረት ከሆኑት ውስጥ አንዱ እንደሆነና ሁሉም ኢትዩጵያዊ የሚኮራበት እንደሆነ የታወቀ ነው። የትግራይ ህዝብም በክፉም በደጉም ወቅት ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር አብሮ ተፈቃቅሮ ፣ ተጋብቶ ፣ ተዛምዶ ኖሯል። የትግራይ ተወላጆች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ይኖራሉ። ይሰራሉ፣ ሀብትና ንብረት አፍርተዋል። አሁን ስልጣን ላይ የሚገኙት እፍኝ የማይሞሉ የህወሃት መሪዎች የከፈልከውን መስዋእትነት ለራሳቸው ስግብግብ ጥቅም በማዋል፣ አሳፋሪ ተግባር እየሰሩ ነው። ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ሊያጣሉህ ይጥራሉ። ሌላውን በጠላትነት እንድታይና እነሱም ጠላትህ እንደሆኑ አስመስለው ያወራሉ። አሁን የተነሳው የህዝብ ትግል በትግራይ ላይ የተነጣጠረ በማስመሰል፣ ገዥዎቻችን ከፋፋይና አደገኛ ቅስቀሳ እያካሄዱ ነው። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነው። በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚካሄደው ትግል፣ የእኩልነት፣ የዴሞክራሲ ፣ የህግ የበላይነት መከበርና ከፋፋዩ ስርአት እንዲያበቃ የሚደረግ ትግል ነው። በዚህ ትግል ተጠቃሚው እነደሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ የትግራይ ህዝብም ጭምር ነው። በስምህ መነገድ በቃ በላቸው። ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘህ በመራሹ ህወሃት ስርአት ላይ ተቃውሞህን በማሰማት ለስርዓት ለውጥ የሚደረገውን የሞት የሽረት ትግል በሙሉ ልብ ተቀላቀል። በአንጻሩም አልፎ አልፎ በጥቂት ሌላውን በማይወክሉ ክፍሎች ሁሉንም የትግራይ ህዝብ እንደጠላት በማድረግ የሚሰነዘረው የጅምላ ፍርደ ገምድል ማጥላላትና በንጹሃን ትግራዮች ላይ የሚካሄድ ማንኛውም ጥቃት ምንም በጎ ጎን የሌለውና ለትግሉም ጠቃሚ እንደማይሆን እናሳስባለን።

**የኢትዮጵያ ህዝብ ያሸንፋል**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋር ትግል ሸንጎ** (SHENGO)
**የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት** (ENTC)
**የኢትዮጵያ ወጣቶች ብሄራዊ ንቅናቄ** (EYNM)
**ለግኑኙነት፤** ENTC contact@etntc.org EYNM ethiorevolution@gmail.com SHENGO **shengo.derbiaber@gmail.com**